# መሬት ለአራሹ!

**ገለታው ዘለቀ**

በአስራ ዘጠኝ ስልሳዎቹ ኢትዮጵያ ደምቃ ነበር። የለውጥ ጥም ይዟት ትጮህ ነበር። መቼም በየሃገሩ አገራዊ ችግሮችን መልክ አስይዞ፣ መሪቃል ወይም መፈክር አውጥቶ ለውጡን የሚመራውና የለውጥ ሃይል የሆነው ወጣቱ ሲሆን በተለይ የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ሁሌም ቀዳሚዎች ናቸው። ታዲያ በዚያ የለውጥ ወራት ጊዜ ከነበረው አንዱና ትልቁ ጥያቄ የመሬት ላራሹ ጉዳይ ነበር አሉ።

መሬት ላራሹ! መሬት ላራሹ! መሬት ላራሹ!.........

ወጣቱ ድምጹን አሰማ ። አራሹ ማን ነው? ያውቋሰኛውና መሬት የለሹ ዜጋ ነዋ። በጥቂት የመሬት ከበርቴዎች እየተጨቆነ የሚኖረው የሰፊው ድሃ ህዝብ ግፍ ይብቃ፣ አዲስ ዘመን መጥቷልና እናንተ የመሬት ከበርቴዎች ሆይ በቃችሁ። አራሹ ገበሬ እጣው በሆነችው በዚህች አገር ውስጥ፣ የርስቱ ገመድ በወደቀባት በዚህች ምድር ላይ መሬት ይኑረው ነው ጥያቄው። በርግጥ ይህ ጥያቄ በጥሩና ሳይንሳዊ በሆነ ሁኔታ የተቀመጠ ይመስለኛል።

በተለምዶ ያ ትውልድ የምንለው ከንጉሱና ከፊውዳሉ ጋር ሳይሰለች ታገለ። ለገበሬው አባቱ ድምጽ ሆነለት። በርግጥ ትግሉ የመሬት ላራሹ ጉዳይ ብቻ ሳይሆን አጠቃላይ የኢትዮጵያን ሶሺዮ ፖለቲካ የሚመለከት ሰፊ የለውጥ ትግል ነበር። ይህ ጥያቄ እንደቀጠለ ብዙ ቆየና በ 1966 ዓ.ም ለውጥ ድንገት ፈነዳ። ሲፈነዳ ባልተጠበቀ መንገድ ነበርና ብዙ ለውጥ ፈላጊ ተማሪዎችን አላስደሰተም። ወታደር ስላፈነዳው በአገሪቱ ስጋቶች አየሉ። ይሁን እንጂ ደርጉ ስልጣኑን በያዘ በማግስቱ የተማሪውን ጥያቄ "መሬት ላራሹን" እመልሳለሁ አለ። የካቲት 25 ቀን 1967 ዓ.ም አንድ ስር ነቀል አዋጅ ታወጀ። መሬት የሰፊው ህዝብ ነው ተባለ። በመሰረቱ ይሄ ሰፊው ህዝብ የሚባል ነገር በውስጡ ሌላ አነስተኛ ህዝብን ያገለለ ይመስላል። በርግጥም በሶሻሊስቶች ትግል ውስጥ የመደብ ትግል ዋናው ነገር ስለሆነ ታጋዮች ለሰፊው ህዝብ ሲሉ ሊበቀሉት የተነሱት አነስተኛ የተባለ መደብ ስላለ ነው። ይህ ግን አደገኛ ነው። ትግል ለሁሉም ነጻነት፣ ለዜጎች ሁሉ ሲሆን ነው ክብ ከሆነ ቄቆና የሚወጣው። ይህ አዋጅ በወቅቱ ቄቁን ለተባለው መደብ ከፍተኛ ለውጥ ነበር። መሬት የሌላቸውን ባለመሬት ያደረገ፣ ከፊውዳል ቄሰኝነት ያላቀቀ ታሪካዊ ለውጥ ነው። ይሁን እንጂ ታዲያ የመሬት ላራሹ ጥያቄ ሙሉ በሙሉ ተመለሰ ማለት አይቻልም። የመሬት ላራሹ ጥያቄ የገበሬውን የባለቤትነት ጥያቄ የሚመለከት ነው። ደርግ ከፊውዳሉ ነጥቆ ባለቤትነቱን ለህዝብ ነው የሰጠሁት አለ። ይሁን እንጂ ህዝብ የመሬት ባለቤት ነው ለማለት በሆነ መንገድ ተደራጅቶ መምጣት አለበት። ይህ ግዙፍ ማንነቱ ደግሞ በመንግስት ነው የሚገለጸው። መንግስት ሲስተም ስላለው በተግባር የሆነ ሃብት ባለቤት ሊሆን ይችላል። በመሆኑም በተዘዋዋሪ መሬት የመንግስት ነው እንደማለት ነው የደርግ አዋጅ። በርግጥ ይህ የመሬት ባለቤት የሆነው መንግስት ለቄቁኑ ለሰፊው ህዝብ የቆመ በመሆኑ የሃገሪቱን መሬት በገመድ እኩል እኩል አካፍሏል። ከዚህ በፊት በፊውዳሉ ስርዓት ውስጡ የበገነው ሰፊ ህዝብ በዚህ አዋጅ ለስሜቱ ርካታ ቢያገኝም ሁሉም እኩል እኩል በመካፈሉ ብዙ ድሆችን ቢያደስትም አጠቃላይ አገራዊ የኢኮኖሚ ተጽእኖው ግን ግራና ቀኝ አልተጠናም። የሆነ ሆኖ መሬትን መንግስት ይዞ አስራ ሰባት አመት ከዘለቅን በሁዋላ ወያኔ መራሹ መንግስት በግንቦት ወር 1983 ዓ.ም አዲስ አበባን ተቆጣጠረ። ህወሃት ለሰፊው ህዝብ ጥቅም ሲባል በረሃ እንደገባ አሁንም ለሰፊው ህዝብ ጥቅም ሲል መንግስትን እንደተቆጣጠረ አዲስ አበባ ላይ ገለጸ። ያ የተንጠለጠለው

የመሬት ላራሹ ጥያቄ ምን ይሆን ይሆን እየተባለ ሲጠበቅ ይህ መንግስት ደግሞ በህገ-መንግስቱ ላይ እንዲህ ሲል አወጀ።

**አንቀጽ** 40

*3. የገጠርም ሆነ የከተማ መሬትና የተፈጥሮ ሃብት ባለቤትነት መብት የመንግስትና የህዝብ ብቻ ነው።*

*መሬት የማይሸጥ የማይለወጥ የኢትዮጵያ ብሄሮች ብሄረሰቦችና ህዝቦች የጋራ ንብረት ነው።*

*4. የኢትዮጵያ አርሶ አደሮች መሬት በነጻ የማግኘትና ከመሬታቸው ያለመነቀል መብታቸው የተከበረ ነው*

ይህ አዋጅ ከየካቲቱ በምን ይለያል? ካልን መሬት የህዝብ ብቻ ሳይሆን የመንግስትም ሃብት ነው የሚል በመሆኑ ነው። ይህንን ጽሁፍ ለማዘጋጀት ከመነሳቴ በፊት ኤንጂነር ይልቃል ጌትነትና ዶክተር በያን አሶባ ለቪኦኤ የሰጡትን ቃለ ምልልስ አዳምጨ ነበር። ሁለቱም መሳጭ የሆነ መልእክት አስተላልፈዋል። ኤንጂነር ይልቃል ስለ መሬት ባለቤትነት ሲናገሩ በሚገባ ገልጸውታል። ህወሃት መራሹ መንግስት መሬት የህዝብና የመንግስት ነው ሲለን ከፍ ሲል እንዳልነው በተግባር ህዝብ የመሬት ባለቤት የሚሆነው በመንግስት በኩል ነው። ከደርጉ የተለየ የመሬት አዋጅ የለም ለማለት ነው።

አንድ ፖሊሲ ወይም ህግ ሲወጣ ከሁሉ በላይ ቶሎ የሚማርከኝ የፍልስፍናው መነሻዎች ወይም መሰረቶች ናቸው። በዚህ በጣም እሳባለሁ። እንዲገባኝም የምፈልገው ያ ነው። መሬት የመንግስትና የህዝብ ነው ብሎ አረፍተ ነገር ማራዘሙ ከደርግ የተሻለ የመሬት ህግ አለ አያስብለውም። ከመነሻው መሬት የህዝብ ነው የሚለው አባባል ራሱ ችግር አለበት። በመሰረቱ መሬት አይደለም የህዝብ መባል ያለበት። አገር ነው የህዝብ መባል ያለበት። መሬት ግን የግል ነው መሆን ያለበት። መሬት የዜጎች ነው መሆን ያለበት። አገር ነው የወል እንጂ መሬት በዜግነታችን እየተዘረዘረ የሚደርሰን የእግዚአብሄር ጸጋችን ነው።

ሁለተኛው ሳቢ ጉዳይ ደግሞ በጣም የተለየ አስገራሚ የፍልስፍና መሰረት ያለው ጉዳይ ሲሆን የዚህ ህግ የፍልስፍና መሰረት ደግሞ መሸጥና መለወጥ አይቻልም የሚለው ነው። እንግዲህ መሸጥ አይቻልም ሲባል መንግስትም መሸጥ አይችልም ባለ መሬቱም መሸጥ አይችልም ማለት ነው። በመጀመሪያ ደረጃ ለምንድነው መሬት ከመሸጥና መለወጥ የኢኮኖሚክ ህግ የወጣው? ምን ግዙፍ ጉዳይ ኢትዮጵያ አገኛትና ነው መሬት እንዳይሸጥ እንዳይለወጥ ያለችው? ብለን የፍልስፍናውን መሰረት እንድንመረምር ያደርገናል። የመንግስት ሰዎች እንደሚሉት አንዱ መሬትን መሸጥ መለወጥ እንዳይኖር የተደረገበት ምክንያት በተለይ በሃገራችን የሚበዛው ገበሬ ድሃ ስለሆነ ትንሽ ሲቸግረው መሬቱን እየሸጠ ይሄድና ሁዋላ ላይ ሄዶ ሄዶ ያንን ጥለነው የመጣነውን የፊውዳሉን ስርዓት መልሰን ቁጭ እንላለን ከሚል ስጋት ነው ይላሉ። ስለዚህም ገበሬውን ለመጠበቅና ሄዶ ሄዶ ሊፈጠር የሚችለውን የመሬት ከበርቴ ስርዓት ለመከላከል መሬት የማይሸጥ የማይለወጥ ሃብት መሆን አለበት ይላሉ። በመሰረቱ የፊውዳሉ ስርዓት የሚመለሰው አንዳንድ ገበሬዎች ብዙ መሬት እየገዙ የመሬት ሃብታም ስለሚሆኑና ያ የሸጠው ገበሬ የነዚህ የመሬት ሃብታሞች የቀን ሰራተኛ ስለሆነ አይደለም። የፊውዳሉ ስርዓት ሊመለስ የሚችልበት እድል የለም። ከሁሉ በላይ ግን ሃብታም እየሆኑ የሚመጡ ገበሬዎች ሌሎች መካከለኛ ወይም ዝቅተኛ ሃብት ያላቸውን ገበሬዎች በእርሻ መሬቶቻቸው ላይ ማሰራት መጀመራቸው የካፒታሊስት ስርዓት መገለጫ ነው። ዋናው መንግስት መጠንቀቅ ያለበት የጉልበት ዋጋን ፍትሃዊነት ማጤንና ሰባዊ መብትን ማስከበር መቻል ነው። ፍትህ ባለበት የካፒታሊስት ስርዓት ውስጥ የሚኖር የሃብት መበላለጥ ላገር ጎጂ አይደለም። በፊውዳሉ ስርዓት ጊዜ ፊውዳሉ ጭሰኛውን እንደፈለገ ያደርገዋል። ድሃው የህግ ከለላ የለውም። ፊውዳሉ ከህግም

በላይ ነው። አሁን ግን የመሬት ከበርቴ ቢፈጠር ይህ ከበርቴ ከህግ በላይ እንዳይሆን መንግስት አለ። የሚቀጥራቸውን ሰራተኞች ተገቢ የጉልበት ዋጋ እንዲከፍል ይገደዳል፣ እንዲያከብራቸው ይገደዳል:: በመሆኑም የመሬት ሃብታም ማፍራት ወደ ፊውዳል ስርዓት ኢትዮጵያን አይመልስም። ከፍ ሲል እንዳልኩት የህግ የበላይነት ስለሚኖርና መንግስትም ህግን የማስከበር ሃለፊነት ስላለበት ይህ አይፈጠርም።

ሌላው በጣም ጉልህ ችግር ደግሞ ኢኮኖሚያዊ ችግሮቹ ናቸው። በኢኮኖሚክስ ውስጥ መግዛትና መሸጥ ዋና ጉዳዮች ናቸው። እነዚህ ከሌሉ ገበያ የለም ማለት ነው። ገበያ ከሌለ ደግሞ እድገትን ማሰብ አይቻልም። ፈጠራን ማሰብ አይቻልም። መሬት ለሽያጭ አይቀርብም ማለት ዲማንድ አይታሰብም ማለት ነው። ገበሬው እርሻን የማስፋፋት ፍላጎቱ ይገደባል አይታሰብም ማለት ነው። ግብዓቶችን ተጠቅሞ በዚያች አንድ ሄክታር መሬት ላይ ካመረተ በሁዋላ ምርቱ ጥሞት ሁለት ሄክታር ባደርገው የበለጠ ምርት አገኛለሁ ብሎ እንዳያስብ ተገድቧል ማለት ነው። በገበሬውና በገበሬው መካከል መሸጥና መለወጥ አይኖርም ማለት ገበያን ከገበሬው ህይወት ማውጣት ነው። በአንድ ኢኮኖሚ ውስጥ ዲማንድና አቅርቦትን የሚገድብ ህግ ማውጣት ኢኮኖሚ እያዳይንቀሳቀስ ሰንክሎ መያዝ ማለት አይደለምን?። የኢትዮጵያ መሬት ከመግዛትና ከመሸጥ ህግ ሲገነጠል በተለይ እንደ ኢትዮጵያ ባለ በእርሻ ላይ በጣም ጥገኛ በሆነ አገር ላይ ከፍተኛ የሆነ የማክሮ ኢኮኖሚ ተጽእኖ ያመጣል። አንዱ የዚህ ፍልስፍና ግዙፍ ችግር የግብርናውን ኢኮኖሚ የረጋ ውሃ ማድረግ (economic stagnation መፍጠር) ነው። ድንበር ነው እንጂ መሸጥ የሌለበት መሬት በዜጎች መሃል የመሸጥና የመግዛቱ ሂደት መጠፍ ነው ያለበት። መሬት በገበያ ላይ ሲውል ነው ግብርናው የሚያድገው።

ገበሬው የመሸጥና የመግዛት መብቱ ሲነፈግ አንዱ የሚያመጣው ሌላ ችግር ገበሬውን "ቢዝነስ ማይንድድ" እንዳይሆን ያደርገዋል። ከብሮች ያርቀዋል። ይህ ደግሞ በሃገር ደረጃ ሲታይ ተጽእኖው በጣም ጉልህ ነው። በግብርናው አካባቢ ለሚታየው ሰፊ ችግር አንዱ ትልቁ ተጽእኖ ፈጣሪ ጉዳይ ይህ ነው። መሬት የማይሸጥ የማይለወጥ የመሆኑ ጉዳይ ካመጣቸው ቀጥተኛና ተዘዋዋሪ ተጽእኖዎች መካከል አንዱ ገበሬውን የንግድ ሰው አለማድረጉ ነው። ከዚህም የተነሳ እንደሚታወቀው አብዛኛው የዋናዋና ሰብሎች አምራች የሆነው ገበሬ በየዓመቱ ምርት የሚያመርተው ለራሱ ነው። ለዓመት ቀለቡ ነው የሚያመርተው። ከራሱ ያለፈ ሰፊ ራእይ እንዳይኖረው ተገድቧል። በዚያች በያዛት በአማካይ አንድ ሄክታር አካባቢ መሬት ላይ ትንሽ ባቄላ ለሹሮው፣ ትንሽ ስንዴ ለዳቦው፣ ትንሽ ገብስ ለጠላው ወዘተ ያመርታል። እነዚህን ሲያመርት እያሰበ የሚያመርተው የራሱን የአመት ቀለብና በልግ ወይ መኸር ሲመጣ የሚያስፈልገውን ዘር ነው። ወደ ከተማ ሄዶ ትንሽ እህሎች የሚሸጠው እንደ ጨው፣ ስኳር፣ ጋዝ የመሳሰሉትን እሱ የማያመርታቸውን ጉዳዮች ለመግዛት ሲያስብ ነው። የከተማው ነዋሪም የሚኖረው በነዚህ ምርቶች ገበሬው እየተነቃቃ በሚሸጠው እህል ነው። ከዛ ውጭ ገበሬው ሁለገብ የእርሻ ስራን ስለሚያካሂድ አነሰም በዛም ፍላጎቱን ከጓዳው፣ ከጓሮው ነው የሚያገኘው። ይህም አንዱ የገበሬውን የቢዝነስ ሰው አለመሆን የሚያሳይ ነው። ገበሬው በመሸጥና በመግዛት ሂደት ውስጥ አክቲቭ ሆኖ አይታይም። በአንጻሩ በበለጸጉ አገራት የምናየው ደግሞ ገበሬው የሚያመርተው ለራሱ ቀለብ አይደለም። ለቢዝነስ ነው። ገበያ እያጠና በሰፊው እያመረተ ያቀርባል። ገንዘብ ባገኘ ቁጥር እየተነቃቃ፣ የተለያዩ የግብርና ግብዓቶችን እየተጠቀመ ምርቱን ከፍ እያደረገ ይነግዳል። ይሄ ነው እድገትን የሚያመጣው። በኢትዮጵያ ውስጥ መሬት የግል ቢሆን አንዱ ጥቅሙ አንዳንድ ትጉ ገበሬዎች የመሬት ይዞታቸውን ባሰፉ ቁጥር ገበያ ማሰብ ይጀምራሉ። "ቢዝነስ ማይንድድ" ያልነው ጉዳይ ይመጣል። ለመሸጥ፣ ብዙ ብር ለማግኘት ስለሚነቃቁ ምርታቸውን ያሳድጋሉ። የገበያ ዲማንድ እያጠኑ በዚያ ላይ ተመስርተው ምርት ያመርታሉ። ይህ ጉዳይ ደግሞ ምርት እንዲጨምር ከማድረጉም በላይ ገበሬውን ያነቃውና ግብርናው

ዘና ብሎ ቢዝነስ ውስጥ ይገባል። እነዚያ ያቺን መሬታቸውን የሸጡ ሰዎች ደግሞ ተጠቃለው ከተማ ይገባሉ ማለት ኣይደለም። ምን ኣልባትም ከኣንድ የእርሻ ስራ ወደ ሌላ የእርሻ ስራ ሊዘዋወሩ ይችላሉ። ኣንድ ገበሬ እርሻውን ትቶ የወተት ላሞች ገዛዝቶ በዘመናዊ መንገድ እያረባ በዚህ ብቻ ለመኖር ሊመርጥ ይችላል። ወይም በኣንዳንድ ሃብታም ገበሬዎች እርሻ ላይ ተቀጥሮ ከዚያ የሚያገኘው የጉልበት ዋጋ ገቢ በዚያች ኣንድ ሄክታር መሬት ላይ ኣርሶ ከሚያገኘው ገቢ ሊበልጥበት ይችላል። ብዙ ምርጫ ይሰጠዋል ማለት ነው። ሌላው ደግሞ ዜጎች በዚህ ዓለም ላይ ኣለኝ የኔ ነው ሊሉት ከሚገባ ሃብት መካከል መሬት ኣንዱ መሆን ኣለበት። በተለይ ገበሬው የባለቤትነት መብቱ ሲነካ በኣለም ላይ ኣለኝ ሊለው የሚገባውን ሊመካበት የሚገባውን የተፈጥሮ ጸጋ መውሰድ ማለት በመሆኑ ትልቅ የመብት ጥያቄ ኣለበት።

በኣሁኑ ጊዜ ከኣዲስ ኣበባ መስፋፋት ጋር ተያይዞ ገበሬዎች ሲፈናቀሉ ኣንዱ የታየው ችግር እነዚህ ገበሬዎች መሬቱ የነሱ ዓይደለምና ሲፈናቀሉ በመሬት ዋጋ መደራደር ኣይችሉም። የተወሰኑ ኣመታት ምርቶቻቸው ተሰልቶ ነው ትንሽ ገንዘብ የሚሰጣቸው። ያ ገንዘብ ደግሞ ቀሪ ህይወታቸውን ኣይለውጥም ብቻ ሳይሆን የተወሰኑ ኣመታት እንኳን ኣይገፋላቸውም። ኣንዱ መሰረታዊ ችግር ይሄ ሆኖ ሳለ በተጨማሪ ከተማዋ ስትስፋፋ እነዚህን ሰዎችም ወደ ሆዷ ማቀፍ ኣለባት።  ሰባዊነት በጎደለው መንገድ በኣማካይ ስድስት ቤተሰብ ያለውን ኣንድ ገበሬ ትንሽ ብር ሰጥቶ የሄድክበት ሂድ ማለት በጣም ወንጀል ነው። ከተማዋ ስትስፋፋ የምታቅፈው መሬቱን ብቻ ሳይሆን ህዝቡንም መሆን ኣለበት። የከተማ ነዋሪ ኣድርጋ መዝግባ፣ ቤትና ቦታቸውን ሰጥታ ለቀሪ ህይወታቸው የሚችሉትን ስራ ሰጥታ ከተማዋ ብትስፋፋ ቅሬታ ኣይነሳም ነበር። ዋናው ጉዳይ ግን ከፍ ሲል እንዳልነው በመሬት ባለቤትነት ጉዳይ ላይ ከፍተኛ የፍልስፍና ችግር በመኖሩ ነው ኣሁን በተግባር ችግሮች ኣፍጠው እንዲወጡ ያደረገው። በኣጠቃላይ ግን በግብርናው ኣካባቢ ያለውን ትልቅ ችግር ስናይ በዓለም ታሪክ ረጅም ጊዜ የወሰደው የኢትዮጵያ የመሬት ላራሹ ጥያቄ ላለፉት ሃምሳ ኣመታት ያልተመለሰ ኣሁንም ያልተመለሰ ያደርገዋልና የመሬት ላራሹ ጥያቄ በኣዲስ መልክ ሊነሳ ይገባዋል።  በርግጥ መሬት ለኣራሹ ሲባል ለገበሬው ብቻ ሳይሆን ከተሜውም የመሬት ባለቤትነቱን ሊያገኝ ይገባዋል። መንግስት መሬት ኣይሸጥም ይልና  ራሱ ግን በሊዝ መልክ የከተማ መሬትን እየቸበቸበ ከፍተኛ ገቢን ያገኛል። ዜጎች ቤታቸውን ሊሸጡ ሲሉ ጣራና ግድግዳው ተተምኖ እንጂ መሬት መሸጥ ኣትችሉም እየተባለ ላልሆነ ህገ ወጥ ስራ  ይዳርጋሉ::

ህወሃት መራሹ መንግስት ኣንዱ ከፍተኛ የሆነ ገቢ የሚያገኝበት የሀብቱ ምንጭ የከተማ መሬት ሊዝ ነው። በሌላ በኩል ገበሬው የእርሻ መሬት ባለቤትነት መብቱን ተነጥቆ ሳለ መንግስት ኣገር የሚያክሉ ሰፋፊ ለም የእርሻ መሬቶችን ለመሬት ተቀራማቾች በርካሽ ይሰጣል። በኣንድ በኩል የፊውዳሉ ስርዓት እንዳይፈጠር እሰጋለሁ እያለ ገበሬውን ኣስሮ ይዞ በሌላ በኩል ደግሞ ቤልጂየምን የሚያህል መሬት ለመሬት ቅርምት ተዳርጓል።

ወደ ገበሬው የመሬት ይዞታ ጉዳይ ስንመለስ ህገ-መንግስቱ መሸጥ መለወጥ ይከለክልና መንግስት በሌላ በኩል ማከራየትንና ማውረስን ይፈቅዳል። ማውረስ እየተቻለ ኣይሸጥም። ማከራየት እየተቻለ ኣይለወጥም ይባላል። ገበሬው የሚያርሰውን እርሻ እስከ መቼ እንደሚያስተዳድር የጊዜ ገደብ የለውም። ማውረስም ይችላል። ነገር ግን መሸጥ ኣይችልም። ይህ ኣሰራር ገበሬውን ከገንዘብ ከማራቁ ሌላ በጣም ኣምታች የሆነ ህግ ነው። ግዙፍ የሆነው ሃብታችን እንዲህ ግልጽነት በጎደላቸውና በትክክለኛ የፍልስፍና መሰረት ላይ ባልቆሙ ህጎችና ፖሊሲዎች ላይ ሲመሰረት የሚያመጣው ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ችግር ግዙፍ ነው። በመሆኑም ኣዲሱ ትውልድ ይህን የመሬት ጥያቄ እንደገና ኣንስቶ ሊታገልለት ይገባል። ያሳዝናል የመሬት ላራሹ ጥያቄ ዛሬም በኣምሳ ኣመቱ ኣልተመለሰም። የመሬት ፖሊሲዎቻችን በውነት በጣም በከፋ ችግር ላይ ያሉ ስለሆነ ህዝቡ ከመልካም

**ኣስተዳደር ጎን ለጎን ኣንድ ዋና የትግል ጥያቄ ኣድርጎ ሊያቀርብ የሚገባው ጉዳይም ነው። የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎችም የቀድሞ ወንድሞቻቸው ያነሱትን ይህን የገበሬውን መሰረታዊ ችግር ኣንስተው ሊታገሉለትና የሃምሳ ዓመቱን ትግል በድል ሊቋጩት ይገባል።**

**እግዚአብሄር ኢትዮጵያን ይባርክ**

geletawzeleke@gmail.com

[**ኢትዮሚድያ** - Ethiomedia.com]

December 25, 2015